# የመጽሐፍ ግምገማ
# ግንቦት 7 ኢትዮጵያ እኮ ምን? እንዴት?
# ደራሲ ክፍሉ ታደሰ
# ገምጋሚ አለሙ እንዳለ

አቶ ክፍሉ ታደሰ ግንቦት 7/1997 ዓ.ም. የተደረገውን ምርጫ በተመለከተ የተለያዩ ሰነዶችን በመሰብሰብና በራሳቸው አመለካከት በመመርኮዝ ወደ 250 ገጾች ያጠቃለለ መጽሐፍ ጽፈዋል። በዚህ መጽሐፋቸው ወደ የ1984 ምርጫ ያዘነበለው ኢትዮጵያን በብሔረ-ሰብና ቋንቋ ላይ የተመሠረተ መንግሥት እንደነበረ አጠር ባለ መልኩ አቅርበዋል። በተለይም ኦነግ ከኢሕዴግ ጋር ተወዳዳሪ በመሆን የ1984 ምርጫ እንደተሳተፈ ሆኖም ግን ኢሕአዴግ ቀስ በቀስ እየሸረሸረ የኦነግን አባላት ማሰር፤ መግደል፤ ከመንግሥት እርከኖች ማውረድ በመጨረሻም ድርጅቱን ሕገ-ወጥ ብሎ እንዳባረረ ጠቁመዋለ። የዚህ የ1984 ዓ.ም. ሂደት በግንቦት 7/1997 ዓ.ም. ከተካሄደው ጋር በተወሰነ መመሳሰልና ዝምድናም እንዳለው ጠቁመዋል።

አቶ ክፍሉ ታደሰ ኢትዮጵያ በአሁኑ ሰዓት (ጊዜ) ሁለት መንግሥት ያላት የመጀመሪያው ከመለስ እስከ ሚኒስተሮችና የቢሮ ዳርከተሮች የሚዘልቅ ሲሆን ሁለተኛው ደገሞ የህወሃት የሥውር መንግሥት (TPLF's Invisible state) ብለው ሰፊ ትንተና በማቅረብ የወያኔን ስውር መንግሥት እርቃነ ሥጋውን ያሳዩበት ነው። ይህ ሥውር ያለሆነው የመለስ ሚኒስተሮች ለሁለተኛ የወያኔ መንግሥት ሽፋን ሠጪ፤ መከታ፤ አገልጋይ፤ መሣሪያ ማደናገሪያ፤ ወዘተ በመሆን የተዋቀረ ኢትዮጵያውያን ሆኑ ዓለም አቀፍ ህብረተሰብ የሚያውቀው በጠቅላይ ሚኒስተር መለስ የሚመራውን ነው። ይህ የወያኔ ሥውር መንግሥት ከጠቅላይ ሚኒስተሩ እስከ ቀበሌ፤ ተራ ወታደር፤ የገበሬ ማህበራት ድረስ ራሱን ችሎ የተዋቀረና የሰለላ ድርጅቱንም በነዚህ ተቋማት ውስጥ አዋቅሮ የሚሠራ ባለሥልጣን ያሉት ግዙፍ ድርጅት እንደሆነ በሚገባ ለአንባቢ አቀናብረው አቅረበውታል። ይህ ከጠቅላይ ሚኒስተሩ መለስ ዘናዊ ጀምሮ ከላይ ወደታች፤ ከታች ወደ ላይ ጥንካሬ ባለው የተዘረጋው መዋቅር ዋናዎቹ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፤ የማስታወቂያ ሚኒስቴር፤ የወታደርና የሰለላ ድርጅቶች፤ የመንግሥት የህግ አውጪ ክፍል፤ የፍትህና የሥራ አስፈጻሚ በዚሁ በወያኔ የስውር መንግሥት ያላቸው ሥልጣን ገደብ የሌለው እንደሆነ አስረድተዋል። ይህ የወያኔ ሥውር መንግሥት በዘመናዊ አሠራር በተዋቀረ መልክ ከ4 ቢሊዮን ብር በላይ የአገሪቷን ካፒታል ያካበተ ራሱን የቻለ መንግሥት እንደሆነ የዲፕሎማሲውን ሥራ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እስከ ኤንባሲ ድረስ ፈላጭ ቆራጭ ይኸው የስውር መንግሥት እንደሆነና በግራ እጁ ዲሚክራሲን በቀኝ እጁ ደግሞ የትግራይ ብሔረተኛነትን የተሸከመ/ያነገበ መንግሥት መሆኑን ወደ ዘጠኝ ገጾች በመስጠት ደራሲው የተቃዋሚው ኋይል በሚገባ እንዲጠቀምበት አቅርበዋል። ሊደነቁ ይገባል

ሌላው ደግሞ በኦሮሞ ቢሔራዊ ኮንግረንስ (አብኮ) ድርጅት ላይ የወያኔ መንግሥት ያደረሰውን በሚገባ ደራሲው ዘርዝረው አቅረበዋል። በዚህ ድረጅት ላይ የደረሰው ጉዳት በኅብረቱም ላይ ያመጣውን ጉዳትና ድክመት ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ጽፈዋል።

እንዲሁም አቶ ክፍሉ ታደሰ ይኽን መጽሐፍ በአጭር ጊዜ ውስጥ አቀነባብረው ለኢትዮጵያዊያን እንዲነበብ ማድረጋቸው የሚያስመሰግን ነው። የስንጹሑፍ ችሎታቸውን፤ ከልምድ ጋር አቀነባብረው እንደዚህ ያለ መጽሐፍ ስላቀረቡ አንባቢያን ደግሞ ያቀረቡትን በመደገፍ ወይም በመቃወም ሰፊ ውይይት፤ ትችት፤ ክርክር፤ ወዘተ እንዲያደርጉበት ይጋብዛል። የፖለቲካ ጥራትና ብስለት እንዲኖርም ያበረታታል። ይህን ምጽሐፍ ለመገምገም እድል በማገኜቴ ደስተኛ ነኝ። ደራሰው ያልቀምሩት ወይም ከእይታ መራቅ የመነጨ ክስተቶችን ለመጠቆም

እወዳለሁ። የወያኔ መንግስት በከተሞች፤ በገጠር በተለያዩ እስር ቤቶች በሺ.ህ የሚቀጠሩ ወጣቶችን፤ ሺ.ማግሎችን፤ ሴት ወንድ ሳይለይ በስር ቤት ያጎራቸውን፤ የገደላቸዉን፤ ያቆሰላቸውን፤ ወዘተ በዝርዝር አቅርበዋል። የወያኔ አድራጎትም ተጋልጧል። እንደዚሁም የህብረቱና የቅንጅቱ ተወካዮች በተለያያ የምርጫ ወረዳዎች መወዳደራቸውንና ያሼነፉበትን ቀጠናዎች የወያኔ መንግስት በማሰር፤ በመግደል፤ በማስፈራራት፤ በማጭበርበር፤ ወዘተ በተቀነባበረ ፋሺስታዊ እርምጃ እንዴት የህዝብ ድምጽ እንደሰረቀ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ዝርዝረዉ አቅርበዋል እኔም እሰዬዉ አንጀቴ ቅቤ ጠጣ፤ አቶ ክፍሉን አመሰግናለሁ።

ለ1997 ዓ.ም. ምርጫ ሦስት ኋይሎች ኢሕአዴግ፤ ተቃዋሚ ኋይሎችና የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ማህበር ነበሩ። ሁሉም በአገሪቷ ምርጫ ላይ ያስከተሉትን ችግሮች እንደአፈጣጠራቸው ለአንባቢያን አቅርበዋል። የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኋይሎች ኅብረት (ኢዴኋኅ) በ1995 ዓ.ም. እንደተመሰረተ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች አወቃቀር፤ ከአገረ ውስጥና ከአገር ውጪ የሚንቀሳቀሱ በጠቅላላው 15 የተደራጁ የፖለቲካ ድርጅቶችን እንዳቀፈ፤ የጥቂቶችን የስም ዝርዝር ጠቅሰው አቅርበዋል። ኅብረቱ ለ1997 ዓ.ም. ምርጫ መግባቱን ሆኖም የዓለም አቀፍ የምርጫ ህግጋት ላይ በተመሠረተ ቅድመ ሁኔታዎችን (pre-condition) እንደቀረበ ገልጸዋል፤ እነርሱም፡

1= የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከፖለቲካ ድርጅቶች ተወጣጥቶ መመሥረቱን
2= የምርጫ አስፈጻሚዎች ገለልተኛ መሆንን
3= የምርጫ ታዛቢዎች ከዓለም አቀፍና ከሀገር ውስጥ ድርጅቶች የተወጣታ መሆኑን
4= የመገናኛ ብዙሐን ያለአድልዎ ሁሉም ድርጅቶች በእኩልነት መጠቀምን
5= በውጪ አገር የሚገኙ የኅብረቱ አባል ድርጅቶች ሀገር ቤት ገብተው በምረጫው የሚሳተፉበት መንገድ እንዲመቻች እነደነበር ጠቁመዋል።

ደራሲው ክኅብረቱ ምስረታ በኋላ ኢዴፓና መኢአድ ተለይተው ሁለቱም ተራ በተራ ኅብረቱ ላይ አሉታዊ መግለጫ እንዳደረጉና ምረጫው እየተቃረበ ሲመጣም ቅንጅት እንደተመሰረተ የቅንጅትም መመሥረት በኢትዮጵያ ያለውን የኋይል አሠላለፍ እንዴት እንደቀየረው በስፋት አብራርተው አቅርበዋል። በሌላ አንጻር የኅብረቱ ፕሮግራም፤ የትግል ስልት አጠቃቀም የጠላት ኋይሉን እንደጠቀመ በተደጋጋሚ የመጽሐፋ ገጾች ያትታሉ። ደራሲው ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የትግል ስልታቸውን፤ የመዋቅር ጥንካሬአቸውን፤ የዋና ጠላት አፈራረጅን፤ የተበታተነ ኋይልን በጋራ አስተባብሮ ለጋራ ዓላማ መጠቀምን፤ በኅብረትና በቅንጅት መካከል የሥልጣን ፖለቲካ (power politics) እሽቅድድሞሽ ያመጣው ጠንቅ ተተንትኖ መቅረብ ሲገባው ደራሲው የራሳቸውን አማራጭ በግልጽም ሳያስቀምጡ ኅብረት ለወያኔ መንግሥት ከተከላካይነት ወደ አጥቅነት አመቺ ሁኔታን ፈጥሮአል። እንዲያውም በአሁኑ ጊዜ ያለአንዳች ሁኔታ (unconditional commitment) ለኢትዮጵያ ልዑላዊነት የሚታገሉትን ድርጅቶች (ኅብረትና ቅንጅት) ተቀራርበው እንዳይሠሩ አንዱ አንደኛውን የሚያጠፋ አስመስሎ የቀረበ የፖለቲካ ትንተና ነው።

እኔ እንደተገነዘብኩት ኅብረት ከተመሠረተ በኋላ ኢዴፓና መኢአድ ከኅብረት መውጣት የታመቀ ኋይልን፤ በቁሳቁስ፤ በገንዘብና በተለያዩ የህብረተ-ሰብ ክፍሎች ለመድረስ አቅም ማጣትን ወዘተ አስከትሏል። ገና ከመጠንሰሱ በኅብረት ውስጥ መከፋፈልን አስከትሏል። ከኅብረት ከወጡ በኋላ ተቻችሎ በጋራ ከኅብረት ጋር ከመሥራት ይልቅ እንደዋና ጠላት በመፈረጅ ሁለቱም ድርጅቶች ከፍተኛ ጉዳት በህብረቱ ላይ አድርሰዋል። ለምሳሌ አቶ ኋይሉ ሻወል “ ------ ከአገር ውጪ የሚገኙት ም/ሊቀመንበሩ የኢሕአፓው ተወካይ አቶ ፋሲካ በለጠ የኅበረት አመራርን ይቆጣጠራሉ

---- በብሄራዊ ሎተሪ አዳራሽ በተጠራው ስብሰባ ኅበረቱ ድርጅቶችን የሚያዳክም ብሎም ህልውናቸውን የሚፈታተን እንቅስቃሴና የመበታተን ድርጊት እየፈጸመ ነው ሲሉ ለታዳሚው አሳወቁ።'' (ገጽ 41 ) እነዚህ ሁለት ደረጅቶች መወጣት ብቻ ሳይሆን በተቀነባበረ መልክ ኅበረቱን በተለያየ ጊዜ ኋይለኛ ምት እንዲደርስበት ያለአሰፈላጊ ጊዜና ጉልበት እየጠፋ በተከላካይነት እንዲቀጥል አደረገውታል። በሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ዋነኛውን ጠላት (primary enemy) ማን ነው? የሚለው ጥያቄ በሚገባ ተንትኖ አለማወቁ ያመጣው የራዕይ ብዥታ ነው።

ይህ በእንዲህ እያለ አቶ ክፍሉ ታደሰ ለግንቦት 7 ምረጫ መሳተፍ ኅብረቱ በአቀረባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ከኢሕአዴግ ጋር እየተደራደረ ያገኛቸውን ውጤቶች ፋይዳቢስ፤ ድርድሩ ረጅም ጊዜ የፈጀ፤ ያመጣው ጥቅም በምርጫው ላይ የረባ ጫና የማያደረግ አድርገው ያቀረቡታል። ''ምርጫ ሊቃረብ ጥቂት ሳምንታት ሲቀረው ከቀረቡት ጥያቄዎች መሃል የተወሰኑትን ለምሳሌ የመንግሥት ሚዲያ አጠቃቀምን፤ የውጪ ታዛቢዎችን ማስገባትንና የመሳሰሉትን ---- እነዚህ ጥያቄዎች በአለቀ ሰዓት ላይ ተሟሉም አልተሟሉም በምርጫ ላይ የረባ ጫና አያሳድሩም።'' (ገጽ 39-40) ሲሉ በኅብረቱ ላይ ለተለያዩ አንባቢያን አሉታዊ አመለካከት ያሳያሉ። ኅብረቱ በውስጡ የነበሩ ሁለት ድረጅቶች ተለይተው ያመጡበትን ድክመት ችሎ ከዚህ የህዋሃት ሰውር መንግሥት ጋር ተደራድሮ ያስመጣውን ገንቢ ውጤት ጥቁር ነጥብ ጥለውበታል። ሚዛናዊ ያልሆነ ግምገማ አሳይተዋል። በጣም የሚያስገርመው ደራሲዉ እራሳቸዉን በራሳቸው ሲቃረኑ በምዕራፍ 4 ኅብረት ከኢህአዴግ ጋር ተከራክሮ ያዘጋጀውን ሜዲያ ቅንጅት ተጠቀመበት ይላሉ። ከዚህ በፊት የመንግሥት ሜዲያ ተሟላ አልተሟላ እያሉ ያናናቁት ሲሟላ በራዲዮና ቴሌቪዥን የአየር ሰዓት ተመድቦላቸው ይኽን የወያኔ ሥውር መንግሥት ተቃዋሚ ኋይሉ እራቁቱን አሰቀረው እያሉ አተቱ። ደራሲውም በዚህ መጽሐፋቸው "ይህ በዓይነቱም ሆን በአቀራረቡ የተለየ የነበረው የፖለቲካ ፓርቲዎች ክርክር፤ ገና አህዱ ሲባል ጀመሮ የሕዝቡን ቀልብ ሳበ። በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች ክርክሩ በሚደረግበት ጊዜ ከቴለቪዥን ጋር ተጣብቀው ይዉሉ ጀመር።'' (ገጽ 59) ይህ የብዙሐን መገናኛን የመጠቀም ለአነስተኛ ጊዜም ቢሆን ሕብረት ከወያኔ መንግስት በድርድ ያስግኘዉ ነበር። አንድም ቦታ አፋቸውን አምልጧቸው የኅብረቱን ጠንካራ የትግል ስልት፤ ታክቲክና እስትራተጅ (tactic & strategy) አንሰተው እሰየው ያሉበት ቦታ የለም። እንዲያው ለምን ይሆን?

ኅብረት ምርጫ ፺፯ ሂደት፤ ክንዋኔና ውጤት በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ኋይሎች ኅብረት (ኢዴኋኅ) እይታ በሚል ርዕስ ባለ 47 ገጽ ግምገማ አድርጓል። ኅብረቱ በመመሥረቱ የተገኙ ድሎች፤ ድርጅቱ ከተመሠረተ በኋላ መሥራች አባል ድርጅቶች መከፋፈል ያስከተለው ጉዳት፤ ህብረቱ ራሱ ባደረጋቸው ድክመቶች፤ የግንቦት ፯ ምርጫ በድል አድራጊነት እንዲያበቃ የተተለያዩ የትግል ስልቶችን በመንደፍ ከቅንጅት ጋር በጋራ ለመሥራት ያቀደውን፤ በጋራ ሆነው የሠሩትን፤ ከሥራ ላይ ሳይውል እንደተንጠለጠለ የቀረ መታገያ እንዴት እንደቀረ ያስረዳል። ኅብረት ከህዋሃት ሰውር መንግሥት ጋር ባደረገው ድርድር ከ8 ማሻሻያ የሃሳብ ነጥቦች ድሎቹን በዚህ መልክ ያቀርባል። ''ገዢው ፓርቲና ተቋዋሚው ክፍል ቀጥተኛና የፊት ለፊት ክርክር ማድረግ መቻሉ ምርጫውን በተመለከተ ---- በገዢው ፓርቲና በተቃዋሚው መካከል ያለውን ልዩነት ሕዝብ ጠንቅቆ እንዲረዳ አስችሏል።'' (ገጽ 7) እንደዚሁም በኢሕአደግ የምርጫ ሕግ አንቀጽ 38/ሠ መሠረት የፓርቲ ተወዳዳሪ 500 የደጋፊዎች ፊሪማና በግል ተወዳዳሪ ደግሞ 1000 የደጋፊዎች ፊሪማ ማቅረቡ እንዲቀር የዚህም ጠቀሜታ የኅበረቱ ባለ47 ገጽ እንዲህ ሲል ያትታል ''የፓርቲ ተወዳዳሪዎች የሰጧቸውን የደጋፊዎች ስም ዝርዝር በመጠቀም ገዢው ፓርቲ አስቀድሞ ማን የማን ደጋፊ እንደሆነ በመለየት በፈራሚዎቹ ላይ ልዩ ልዩ ጫና ማድረግና መራጨች በነጻነትና በሚስጥር ምርጫውን እንደፈለጉ ከፍተኛ ተጽእኖ ያደርግ ስልነበር'' (ገጽ 7) እንዳስቀረ ያስረዳል።

ኢሕአፓና አቶ ክፍሉ ታደሰ (እሳቸውም በውስጡ ስለነበሩ) ብቻ የህዋሀት አመሠራረት፤ አስተዳደግና፤ ባህሪ ወዘተ በሚገባ ጠንቅቀው ያውቃሉ ። ማወቅ ብቻ ሳይሆን እንደ ኢሕአፓ በአሁኑ ጊዜ ከሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ደርጅቶች ሁሉ ስለወያኔ ሥውር መንግሥት የሚያውቅ ለአሳር ነው። ኢህአፓ የዚህን ሥውር መንግሥት በዴሞክራሲያ፤ በፍኖተ ራዲዮ፤ በተለያዩ መጽሔቶች፤ የፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ሰነዶች (documents)፤ በሕዝባዊ ስብሰባዎች ወዘተ በዝርዝር አስተምሯል። በዚህ ከይሲ የፖለቲካ ድርጅት (ህዋሀት) ላይ አቅሙ ከሚፈቅደው በላይ የፖለቲካ አቋሞቹንና ፖሊሲዎቹን አጋልጧል። ያለምንም ማመንታት የኢትዮጵያ ህብረተ-ሰብ ነቅቶ እንዲከታተልና እንዲጠባበቅ አንቅቷል። ኅብረቱ ከግንቦት ምርጫ በፊት የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ከፖለቲካ ድርጅቶች ተወጣጥቶ ይመስረት ብሎ ሲከራከር የነበረውን ደራሲው ቦርዱ ምን ያህል ግዙፍና ሰፊ ድርጅት እንደሆነ ይህንን ድርጅት መወዳድር ሊወጡት የማይቻል ተራራ አስመሰልው በገጽ 38 ላይ ያቀርባሉ።

በመጽሐፉ አጋማሽ አካባቢ ደግሞ የማጣራቱ ሁኔታ ሲከሽፍ "ህጋዊ አግባቡ የትም ሊያደርስ እንድማያስችል የውጭ ታዛቢዎችም ጭምር ተገነዘቡ። ወገንተኛ የሆነ የምርጫ ቦርድና ፍርድ ቤት ባለበት ሁኔታ በህጋዊ መንገዶች ውጤት ለማምጣት መሞከሩ የሚያዋጣ አይደለም ብሎ በመገመት፤ የተቃዋሚ ኋይሉ የቦርዱን ውጤት ይዞ ወደ ፍርድ ቤት ላለመሄድ ወሰነ" (ገጽ 139) ብለው ያሰቀምጡታል። የአውሮፓ አንድነትና የካርተር ማዕከል በኢትዮጵያ የተካሄደው ምርጫ የዓለም አቀፍ መሥፈርትን ያላሟላ እንደሆነ በዝርዝር የቀረበው በዚህ የምርጫ ቦርድ ወገንተኛ መሆኑ እየታወቀ፤ የኅብረቱም አቋም ቅድመ ሁኔታዎች እንዲሟሉ ብሎ መታግሉ እየታወቀ፤ ኅብረቱን በህብረተሰባችን እንዳይታቀፍ፤ ጥርጣሬ እንዲያስከትል፤ እንቅፋት እንደሆነ ከአጭር ጊዜ ብቻ ሳይሆን ከረዥም ጊዜ አጋር ቅንጅት ጋር አብሮ እንዳይሠራ፤ አካለ ስንኩል (disable) የተደረገ ጽኑ አመለካከት ደራሲዉ አሳይተዋል። የውጪ ታዛቢዎች ምርጫውን እንዲታዘቡ በህብረት ያለመሰልቸት የተገኘ የድርድር ድል ነው። ይኽንንም ድል የባለ 47 ገጽ ምርጫ ፺፯ ግምገማ እንዲህ በማለት ያቀርበዋል። " የውጪ ታዛቢዎች ምርጫውን እንዲታዘቡ ማድረግ---- በአንድ በኩል የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጋድሎና ድል በሌላ በኩል የገዢው ፓርቲ የማጭበርበር ሙከራ ይፋ እንዲሆንና በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲታወቅ አስችሏል።" (ገጽ 7)

በአቶ ክፍሉ ታደሰ እይታ/ራዕይ ሕብረት የረባ ጫና የማያሳድር፤ የቀሰተ ደማና ፍንጣቂ እንኳ ያልደረሰው፤ ለህወሃት መንግሥት "ማስፈራሪያ" በመሆን ያገለገለ ነው። በጣም ያስገረመኝ አንድም ቦታ (ገጽ) አፍ አምልጧቸው እንኳ በግልጽና በተጨባጭ ኅብረቱ የትግል ስልቶች መሆን ያለባቸው ብለው አማራጭ የትግል ሂደት ያቀረቡት የለም። እንዲያዉም የተገላቢጦሺ ደራሲዉ የህብረቱን ፕሮግራም በተምታታ ህሳባችዉ እንዲህ ሲሉ ያቀርባሉ "ምርጫ የዲሞክራሲ አንዱ አካል እንደመሆኑ በሀገሪቷ የፖለቲካ ፓርቲዎች መጎልበት፤ የሲቪክ ድርጅቶች መጠናከር፤ የሕዝቡ የዲሞክራሲ ባህል ማደግና በመሳሰሉት የሚለካ እንደመሆኑ መጠን፤ በረዥም ጊዜ ሂደትና ሊከማች በሚችል ድል እንጅ በአንድ ፕሮግራም የሚቀየር አለመሆኑን መረዳት ለማንም የሚከብድ አይደለም።" (ገጽ 183) ከዚህ ላይ በደራሲው አእምሮ ሁለት የተቃረኑ አመለካከቶች ይታያሉ። በአንድ በኩል የወያኔ ሥውር መንግሥት በፖለቲካው፤ ሥነ-ልቦናው፤ በድረጅት አወቃቀሩ፤ በስለላና ወታደራዊ መዋቅሩ ግዙፍ እንደሆነ ያቀርባሉ። በዚህ መጽሀፋቸው እስከ መቶ ዓመታት ለመግዛት ሃሳብ እንዳለውም ጠቀስ አድርገው ያልፋሉ። ታዲያ እንደዚህ ያለ ግዙፍ መንግሥት ጋር ለመታገል ገና የፖለቲካ ድርጀቶችም አልበሰሉ፤ የሲቪክ ድርጅቶችም አልጠነከሩም፤ የሕዝቡም ዲሞክራሲያዊ ባህል አላደገም እያሉ በሌላው አእምሮአቸው ያስተምሩናል። የወያኔ ሥውር መንግሥትም የሕዝቡ ዲሞክራሲያዊ ባህል አላደገም፤ የፖለቲካ ኋይሎች አብረው ከመሥራት ይልቅ አክራሪ ሁነው መንግሥቴን ይተናኮላሉ፤ የሲቪክ ድርጅቶችም አላደጉም እያል ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለዓለም አቀፍ ህብረተ-ሰብም ደጋግሞ የብልጠት ቅሰቀሳ አድርጓል። ተጠቅሞበታል። እንግዲህ እርስዎንም ዕድሜ ይስጥዎትና የወያኔ መንግሥት ከመቶ

ዓመታት በኋላ ሲያከትም የፖለቲካ ፓርቲዎች፤ የሲቪክ ድርጅቶች፤ የሕዝባችንም የዲሞክራሲ ባህል ያድጋል። እንደዚያማ ከሆነ የፖለቲካ ብስለት፤ ራዕይ የተከማቸ፤ ልምድ አፈር ድሜ በላች!

ደራሲው የወያኔን የስውር መንግሥት ከግንቦት ምርጫ ጋር በማዛመድ እንዲህ ያስቀምጡታል። "የስውር መንግሥት አሠራር እስካለ ድረስ የኢትዮጵያ ህገመንግሥት ይሰራል ብሎ ማሰብ ከቶውንም የማይቻል ነው። የዚህ ስውር መንግሥት ገበና አደባባይ ወጥቶ ካልታወቀና እንዳይሠራ ካልተደረገ በኢትዮጵያ ምርጫ ይሰራል ብሎ ማሰብ ዘበት ነው። የስውር መንግሥት እስካለ ድረስ ከህወሃት እጅ የፖለቲካ ሥልጣንን በምርጫ አማካኝነት ፈልቅቆ ማውጣት የማይታሰብ ነው። ለዚህም የ1997 ዓ.ም. ምርጫ ምስክር ነው።" (ገጽ 159) ሠረዝ የኔ ነው። የቅንጅቱ አመራር በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ዋና ጠላት ማን ነው የሚለው አልተገለጸም፤ እንዴትስ ገበናውን በአደባባይ እናጋልጠው ለሚለው የመታገያ ስልቶች አልተነደፈም፤ የስውር መንግሥቱ ሊደመሥሠው የማይችል መዋቅር በህብረተሰቡ ውስጥ አልተጣለም። እነዚህ ድክመቶች በቅንጅት ውስጥ በጉልህ መታየታቸውን ደራሲው ቅልስልስ ብለው የጠቆሟአቸው ወሳኝ መተክል በምርጫ ወቅት ላይ ጉልህ ጉዳት አስከትለዋል። የእኔ አነሳስና ከጸሃፊው የጠበኩት የሁሉንም ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ጥንካሬና ድክመት በሃቅ ያቀርባሉ ብዬ ነበር፤ ነገር ግን ሽፋፍኖ ማልፍ ውግንተኝነትን አያሳይም ወይ? ለትግሉስ ጠቃሚነቱ የት ላይ ነው?

በተጨማር ደራሲው የወያኔ ስውር መንግሥት የሥነ-ልቦና ጦርነትን እንዴት እንደተጠቀመ ከተቃዊሚው አባላት እንደነ አቶ ልደቱ በመጀመሪያው ክርክር ላይ የትግራይ ነፍስ ወከፍ ድጎማ ለሌላው ክልል ከተመደበው ይበልጣል ያሉትን (አቶ ልደቱ ያቀረቡት በሌላ የውጭ አገር ሰው በቀረበው ሰነድ ላይ ተመርኩዘው ነው ስህተት የለባቸውም) በነገራችን ላይ አቶ በድሩ አደም ባደረጉት ንግግር ወደመጡበት እንመልሳቸዋለን በማለት የተጠቀሙበትን ቅስቀሳ ወያኔ በዘዴ ካፒታላይዝ እንዳደረገው ጠቁመዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በእኔ እይታ፡
<u>አንደኛ</u> በተለያየ ዘዴና ብልሃት የወያኔ ስውር መንግሥት የተቃዋሚውን ኀይል እያዋከበ በነበረበት ጊዜ የቅንጅት አመራር የሥልጣን ሽኩቻ ሙሉ በሙሉ ተውጦ ምንም የተከላካይነት ምላሽ አያደርግም ነበር። አንድ ቡድን ወይም ድርጅት በውስጡ በዘር፤ በሃይማኖት፤ በጎሣ፤ የሥልጣን ሺሚያ ወዘተ ሲከፋፈል አካል ሰንኩል በመሆኑ በራሱ፤ በአባላቱ፤ በደጋፊዋቹ ወይም ቀመንልሃል እያሉ በአሰባሰቡት ሕዝብ ላይ መቀበል የማትችለውን የጠላት ኋይል ያሳርፋበታል። ገና ከመጀመሪያው ኢዴፓና መኢአድ ከኅብረት እንዳፈነገጡ በዋና ጠላትነት ኅብረቱ ተደርጎ ከፍተኛ ቅስቀሳና ወቀሳ አድረገውበታል። <u>ዋና ጠላት ማን ነው</u>? <u>የትግል አጋሮቹ እነማን ናቸው</u>? የትትግል ስልታችን ምንና እንዴት መደረግ አለበት? የአጭርና የረጅም ጊዜ ግባችን መን መሆን አለበት? ተበሎ የተነደፈ ነገር የለም። ይህ የስውር መንግሥትንና የትግል አጋር ድርጅቶችን እኩል አድርጎ መመልከት ወሳኝ የትግል ስህተት ነው። በሆነ ምክንያት ከኅብረቱ ከተወጣ በኋላ ተመልሶ አሁንም ዋና ጠላት ይኸው የወያኔ ስውር መንግሥት መደረግና ያለ የሌለ የጉልበት፤ የገንዘብ፤ የዕውቀት፤ ችሎታ፤ ወዘተ... በሁሉም አቅጣጫ ቀይሶ መታገል ቀረቶ የትግል አጋር ድርጅት ላይ ማነጣጣር ሆነ። በቅንጅት መሪዎች መካከል ያለው የሥልጣን ሺሚያ ከትግሉ ዋነኛ ሆኖ የበላይነቱን ያዘ። ደራሲው ስለዚህ የሥልጣን ሽኩቻ እንዲህ ይሉታል። " መኢአድና ኢደፓ ቅንጅትን ከመቀላቀላቸው በፊት ለመዋሃድ ሞክረው ሊሳካላቸው እንዳልቻለ....ሁለቱ ድርጅቶች መካከል በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ልዩነቶች የተነሱ ቢሆንም በጣም አስቸጋሪና አሳሳቢ የነበረው በቅንጀት ስም እጩዎችን ለማቅረብ ይደረግ የነበረው ሂደት ውስጥ የተነሳው ከፍ ያ ልዩነት ነበር።" (ገጽ 189) ኅብረት የህወሃት/ኢሕአድግ መንግሥት በሰላማዊ ሕዝብ የተባበረ ትግል እንዲወገድ ብሎ የታገለበትን ደራሲው ጠላት ለአጸያፊ መቀስቀሻ ተጠቀመበት፤ ቅንጅቱም ከሚችለው በላይ የስነ-

ልቦና ጦርነት ጠላት አደረገበት፤ ምቱንም መሸከም አልቻለም። ለዚህም ተጠያቂው ኅብረት እንደሆነ ተደርጎ ተገመገመ። በቅንጅቱ ውስጥ የተፈጠረው ውስጣዊ ቅራኔ እንደዋና/ወሳኝ አልተወሰደም። የቅንጅቱ መሪዎች ዋና ጠላት ማን ነው? የሚለውን አተናተን ከነባራዊ ሁኔታ ጋር አዛምደው አልተመለከቱትም። የወያነን የስውር መንግሥት ባሕርይና የፖለቲካ ውስብስብነት ደራሲው እንደተገነዘቡት ለ14 ዓመታት አመራሩ አላጤውም። ይህም በደራሲዉ በጣም ተልፈስፍሶ ተገምግሟል። በቅንጅት አመራር የሥልጣን እሽቅድድም ቀስተ ደመና በመጀመሪያዎቹ ግጭቶች አስታራቂ እንደነበረ በኋላ ግን ከመኢአድ ጋር እየተቀራረበ አቶ ልደቱ የሥልጣን ጥማቸውን ደርቆ እንዲቆም እንዳደረጉት ከቅንጅት ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበር እስከተለያዩ የሥልጣን እርከኖች አለመመረጣቸውን (አቶ ልደቱን ማለት ነው) በገጽ 200 እና 2001 ያስረዳል። እንዲያውም ኢዴፓ ከሁለት ተከፍሎ አንደኛው ክፍል ከቀስተ ደመና ጋር መዋሃዱን አቶ ለደቱ ሲሰሙ የበለጠ እንደተበሳጩ ያብራራል። በኢዴፓና (አቶ ልደቱ) በቀስተ ደመናው (ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ) መካከል ከዚህ በፊት ያልነበረ የሥልጣን ግጭት እየጠነከረና እየሰፋ መሄዱን ደራሲው ያስረዳሉ። እኔ እንደተረዳሁት በነዚህ ድርጅቶች ውስጥ የተፈጠረው የሥልጣን ሽኩቻ እጅና እግራቸውን ጥፍር አድርጎ አስሯቸዋል። ያ የወያኔ ሥውር መንግሥት አደገኛ ቦዘኔ ወጣት እያለ ያዋከበው፤ ቅንጅት ሥራ እንፈጥርልሃለን ያለው፤ ያ በንግድ ህብረተሰብ ተሰፋ አድርጎ የተሰበሰበው፤ ያ የባህር በር እንከፍትልሃለን ያሉት ወዘተ... ሁሉ ተረስቶ የሥልጣን ትግል ምርኮኛ ሆኑ። የቅንጅት አመራር በእደዚህ በሽታ ተለክፎ በምን ቋንቋ ከኅብረት ጋር በሁሉም የትግል ስልት መቀየስ ይቻላል? እንዲያው ለምን ይሆን ደራሲው እንደወሳኝ ታግሎ መታገያ ማየት የተሳናቸው? ገና ከመጀመሪያወው ከኅብረትቱ ጋር አብሮ አለመሥራት ለካስ የሥልጣን ኮርቻ አስክሮአቸው ነው። ደራሲውም የራሳቸውን መርህ ከቅንጅት ጋር አዛምደው እየቀመሙ ያቀረቡት ኅብረቱን አካለ ስንኩል ከተቻለ ቀስ እያለ እንዲከስም (wither away) በማድረግ የተቃኘ እንጅ በቅንጅት ውስጥ የተደረገው ቀጣይነት ያለው የሥልጣን ትግል ዋንኛ/ወሳኝ ችግር ለምን ለዘብተኛ ሆኖ ቀረበ?

<u>ሁለተኛው፡</u> መሠረታዊ የቅንጅት ደካማ ጎን ታግሎ የሚያታግል <u>ታክቲክና እስትራተጅ</u> አለመኖሩ ነው። የወያኔ ስውር መንግሥት ያለ የሌለ ኃይሉን አቀነባብሮ በሁሉም አቅጣጫ ሲያዋክባቸው አንድም ከኅብረት ጋር ሆነው በሙሉ አቅምና ልብ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ መጠቀም ብሎም ማጥቃት አልቻሉም። እንዲያውም ከኅብረቱ ዘንድ አነሳሽነት ሲመጣ ማመንታት በኅብረቱ መመራት የሉብንም እየተባለ መታገያ ሲልቱን ወዲያውኑ መርምሮ ከተከላካይነት የሚላቀቁበትን እይታ መተለም አልነበረም። ደራሲው ይህ የትግል ስልት እንደሌለ እየተገነዘቡ ኅብረቱም በኦሮሞ ኮንግረስ ላይ የወያኔ ስውር መንግሥት ያደረሰበት ጥቃት በዝርዝር እያስረዱ ከዚያም የዶ/ር በየነ ጴጥሮስ ከኅብረቱ ማፈንገጥ ከፍተኛ ጉዳት እንዳደረሰ እየተገነዘቡ ኅብረቱ የብሔራዊ እርቅ ምስረታን አቀረበ እያሉ ይኮንኑታል። ያ መከረኛ የፖለቲካ ፓርቲዎች አለመደራጀት፤ የሲቪክ ድርጅቶች አለመበልጸግ፤ የሕዝቡ የዴሞክራሲያዊ ባህል አለማደግ ከደራሲው ፊት እየተደቀኑ አስቸግሯቸው ይሆን?

ጸሐፊዉ ስለቅንጅት ታክቲክና ስታቴጅ ጠቅስ ያደረጉትን እንመልከት "ኢሕአደግ በማጥቃት ላይ በተሠማራበት ወቅት ቅንጅት እየተከላከለ ማጥቃት የሚችልበትን እስትራተጅ አልነደፈም። አንድ የቦክስ ተጋጣሚ ባላንጣውን ሊያሸንፍ የሚችለው በመመከት ብቻ ሳይሆን እየተከላከለ ሲመቸው ደግሞ እያጠቃ ጭምር ነው። ..... ሕዝቡ ድጋፍ ኃይል ሆኖ እንዲወጣ ማድረግ ተገቢ ሆኖ ሳለ ያንን ማድረግ አልቻለም።'' (ገጽ 185) ይኸንን ማድረግ የተሳነውን የፖለቲካ ድርጅት ኅብረቱ በውስጡ መከፋፈል ሳይገታ ያቀረባቸውን መታገያ ስልቶች ቅንጅት በቀና መንፈስ እየተባባረና እየቀለጠፈ አለመሥራቱ ሁለተኛው ቁልፍ ደካማ አመለካከት እንደነበረ ደራሲው አልጠቆሙም።

እንዲያውም ህብረቱ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ያቀረባቸውን የትግል ስልቶች የቅንጅቱን አመራር እሥር ቤት አስገባቸው ለማለት ይቃጣቸዋል።

ሶስተኛው ቅንጅት ሁኔታው የሚጠይቀውን መዋቅር በህቡዕ አላሰበበትም። አላጤነበትም። እንዲያውም ቅንጅት "መንፈስ" ነው እያለ የከረመ የፖለቲካ ድርጅት ይመስላል። ዋና ጠላት የወያኔ ስውር መንግሥትን ጠበያት ጠንቅቶ ያልተረዳ፤ የመታገያ የትግል ስልት ያልነበረው፤ እራሱንና አባላቱ ያለ ህቡዕ መውቅር ሳይዘረጋ ለግንቡቱ ሰባት ምርጫ ላይ አሉታዊ አስተዋጽዎ አድረጓል። ደራሲው ቀስተ ደመና በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጸንሦ በቅንጅት ላይ መሠረታዊ ለውጥን ያስመጣ ትንሽ ድርጅት የሚሉት በዚህ የህቡዕ ድርጅት መዋቅር አስፈላጊነት ላይ እንዲህ ብለው ጽፈውታል "እነዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ዙሪያ ያሉ ግለሰቦች ተደራጅተው ትግል ውስጥ ሲገቡ ማንኛውንም ሥራ ህጋዊ በሆነ መንገድ ብቻ ለመሥራት ነበር የወሰኑት። ከባላንጣቸው በኩል ይህን የመሰለ አሠራር በሌለበት ሁኔታ ውስጥ በዚህ መንገድ ለመሥራት ማሰባቸው የዋህነት ነው ሊባል ይችላል። ተበሏልም። ደግሞም ተመክረዋል።" (ገጽ 130)። እንግዲህ ዶ/ር ብርሃኑ ከማንኛውም የቅንጅት አመራር እጅግ የበሰለ ልምድ ያላቸው፤ የወያኔን የስውር መንግሥት ላይ ያላቸው አመለካከት በጣም የለሰለሰ ነው። ታዲያ የእሳቸው የፖላቲካ ትንታኔ እንደዚህ ከሆነ ለቀሩት የቅንጅት አመራር ጠላትና አጋር እኩል ናቸው። ይኸን የወያኔ የስውር መንግሥት ለመጣል ሁለት ነገሮች እጅ ለእጅ አብረው በአንድነት መሄድ አለባቸው። የትግል አጋሩ ሁሉ በአንድነት ሲታገል፤ የመዋቅር ሥራ በሰፊው ሕብረተሰባችን ውስጥ ሲሠራ፤ ሁለቱም ዋነኛ ሥራዎች አልተሠሩም። ታዲያ ደራሲው የመዋቅር አለመዘርጋትን ያክል ትልቅ ቁልፍ ነገር ለቅንጅት አመራር ለመግለጽ መለሳለስ ለምን ተመረጠ?

አራተኛ፡ ወያኔ በፖለቲካ አጭበረባሪነት፤ ከኢሕአፓ፤ ኢዲዩ፤ ኦነግ ፤ ወዘተ ጋር የሚደራደር እየመሰለ ጊዜን ገዝቶ ከተቻለ ተቃዋሚውን ማዳከምና ስንኩል የማድረግ ክፍተኛ ልምድ ያለው የረጅም ጊዜ የሰለላ ልምድ ያካበተ ድርጅት ነው። በዚህ የልምድ ማጣት የተመሠረተ ድርጅት ላይ የጠላት ምት አስመልክቶ የኢዴኣጎን ምርጫ ፺፯ ሂደት፤ ክንዋኔና ውጤት እንደሚከተለው አስቀምጠታል "የአምባገነኖች ትልቁ ችሎታቸው የማይወጡት ተቃውሞ ሲገጥማቸውና ሁኔታው ቀውጢ ሲሆንባቸው እንደሁኔታው ጊዜ መግዛት መቻላቸው ነው። ሲወጠሩ አንገት መቀልበስ፤ ለሰለስ በማለት ጊዜ መግዛት፤ ውስጥ ውስጡን ሁኔታው ለነርሱ እንዲያመች ካደረጉ በኋላ ለተቃዋሚው ፋታ ሳይሰጡ ከማድቀቅና ጭራሹን ለማጥፋት አለበለዚያ ለነርሱ በሚያመች መልክ ጠፍጥፎ ከመሥራት ወደኋላ አይሉም።.... ነብር አዳኝ የመጀመሪያ መመሪያው ነብር አቁስሎ መተው እንደለሌበት ጠንቅቆ ማወቅ ነው። (የቆሰለ ነብር በምንም መንገድ አቁሳዩን ለማጥፋት ወደኋላ እንደማይል የታወቀ ነውና።)" (ገጽ 3) እነዚህ አራት መሠረታዊ ድክመቶች በላቀ መልክ መተንተን ብቻ ሳይሆን ለጠላት ራስን አመቻችቶ መስጠት ያመጣውን፤ አላስፈላጊ መስዋዕትነት (unnecessary sacrifice) መክፈል የጠላት አምባ የሚፈልገውን (የቀየሰውን) እንዲያገኝ አድረጎታል። ከዚህ ቁልፍ ስህተት ያልተማረ የፖለቲካ ድርጅትና የደራሲው ደግሞ አልስልሶ መቃኘት በስህተት ላይ ስህተት ነው። ሌላው ደግሞ ይኸንን መጽሀፍ ለአትመት ከመላኩ በፊት የኅብረቱ ደጋፊዎችም ረቂቁን እንዲያነቡት እንደተደረገ በገጽ 10 ውስጥ ተገልጿል። ደራሲው የስውር መንግሥቱ ሰላዮች እየተቀባበሉ ያዋከባቸውን ለቅንጅት አመራር አባል ሲያጫውቱ እንዲህ ይላሉ "ለአንድ የቅንጅት ከፍተኛ የአመራር አባል አጫወተ ወዳጂም ለምን ከመኪናህ ወርደህ ምንድነው የምትፈልጉት አትላቸውም ነበር አሉ። እኚህ የቅንጅት የአመራር አባል የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥርአት ነፍስ እንዲዘራ በኢትዮጵያ ሕጋዊና ግልጽ አሠራር እንዲሰፍን ከሚታገሉ ሀቀኛ ሰዎች አንዱ ናቸው ብለው ደራሲው ያምናሉ። ይሁንና ከዚህ አነጋገራቸው የህዋሃትን አሠራር እንዴት ሊቋቋሙ እንዳሰቡና ምናልባትም የሥልጣን ፖሊቲካ ገና እንዳልተረዱ ወይም ደራሲው ሊረዳቸው እንዳልቻለ ተገነዘቡ።" (ገጽ 177) ልክ እንድዚህ አገላለጽ የኅብረቱ ደጋፊዎችን ረቂቁ

እንዲያነቡ የተደረጉት ከሀቀኛ ሰዎች አንዱ ሊሆኑ ይችላሉ። ሆኖም የኅብረቱን የውስጥ ፕሮግራም፤ የትግል ስልት እየከለሱ፤ እያንቋሸሹ፤ እያጨማለቁ፤ እየኮነኑ፤ ወዘተ… የተጻፈን መጽሐፍ እንዳለ ከተቀበሉ ከላይ በተጠቀሱት ታጋይ ወዳጄ መልክ አገናዝባቸዋለሁ። የኅብረቱ የትግል ስልቶች ቅንጅቱን አጥፊ ብሎም አመራሮች እሥር ቤት እንዲወርዱ ምክንያት እንደሆነ ተደርጎ የተጻፈ ነው። አንዱ ድርጅት የትግል አጋሩን እንድሚያጠፋ አቀራረብ ካለው በሁለቱ ድርጅቶች (ቅንጅትና ኅብረት) መካከል ያለው ልዩነት እየሰፋ ይሄዳል። እንዲያው በደራሲው መርህና በኅብረት፤ በደራሲው ራዕይና በኅብረት፤ በደራሲው የትግል ስልቶችና በኅብረት ያለው መሠረታዊ ልዩነት (fundamental difference) በኅብረትና ቅንጅት መካከል የተደረገ አስመስሎ መጻፍ የፖለቲካ መሲህነት ነው። ታዲያ እንዴት አድርጎ መተባበር የኢትዮጵያ አንዱ አማራጭ ብቻ መፍተሄ ይሆናል።

በእኔ እይታ አቶ ክፍሉ ታደሰ ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች በተለይም ህብረትና ቅንጅትን ውይንም በውስጣቸው የታቀፉትን የፖለቲካ ድርጅቶች ሚዛናዊ በሆነ መልክ አልገመገሙም። ወገንተኝነትንና አድሏዊነትን (biase) በሚገባ አሳይተዋል። በንደዚህ አይነት አቀራረብ፡ እይታና ግምገማ አገራችን ለምታደርገው የፖለቲካ ትግል ይጠቅማል? ለማንስ?

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ